በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

**የሰበር መ.ቁ 212620**

**ቀን፡- 18/4/2014 ዓ.ም**

**ዳኞች ፡-** ከድር አልይ

ሱልጣን አባተማም

ዋዚሞ ዋሲራ

**አመልካች፡ቾች-** እነ አበበ ጨዶ /26 ሰዎች/ ጠበቃ ሲሳይ ገመቹ ቀረቡ

**ተጠሪ፡/ዎች-** እነ አርባ ምንጭ ዙሪያ ወረዳ አስ/ፅ/ቤት /3 ሰዎች/

መዝገቡ ለዚህ ችሎት 10/12/2013 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 35305 በ ግንቦት 18 ቀን 2013 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት መሆኑን ገልፆ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ባቀረበው ማመልከቻ መነሻነት ነው፡፡ በዚህ መሰረት መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ትአዛዝ ሰጥተናል፡፡

# <u>ትዕዛዝ</u>

ለክርክሩ ምክንያት የሆኑ ይዞታዎችን አመልካቾች 1987 ዓ.ም ጀምሮ በመያዝ ከ 26 ዓመት በላይ ያለው መሆናቸው ተጣርቶ ከሚመለከተው አካላት መግለጫዎች ቀርቦ እያለ ከይዞታቸውና ከንብረቶቻቸው በሚያፈናቅል ሁኔታ እንድለቁ የተወሰነበትን አግባብ የፌ/ጠ/ፍ/ቤትሰበርሰሚችሎት በመ/ቁ 37391፣ 47252፣107217፣77983፣37184፣33945 ከሰጠው የሕግ ትርጎሞች እና መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርሆች እንዲሁም ከክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ጋር በማገናዘብ

መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ ብለናል፡፡

1.መጥሪያ ለተጠሪ/ዎች/ ይድረስ ብለናል፡፡

2. ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክራቸውን በሬጅስትራር ፅ/ቤት በኩል ይቀባበሉ፡፡

3. ቀጠሮ ለ 09/05/2014 ዓ.ም ተቀጥሮአል፡፡ 5፡00 ሰዓት

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ